# *ወገኖቻችን በአገር ቤት ለለዉጥ ዋጋ እየከፈሉ ነዉ - በዉጭ አገር ያለነዉስ ?*

*ግርማ ካሳ*
*(muziky68@yahoo.com)*

*የካቲት 27 2002*

*ግንቦት 15 ቀን 2002 ምርጫ በኢትዮጵያ ይደረጋል። ይህን ምርጫ በተመለከተ የተለያዩ አስተያየቶች ሲሰጡ ሰንብተዋል። ስለዚህ ምርጫ ከአዲስ አበባ የሚመጡ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት በአገር ቤት ያሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች የተከፈተዉን እጅግ በጣም ጠባብ እድል በመጠቀም፣ የምርጫዉን ዘመቻ በተጧጧፊ መልኩ የያዙት ይመስላል። ምንም እንኳን ዘግይተዉ ቢጀምሩም የምርጫ ክርክሮች በመጠኑም ቢሆን እየተሰሙ ነዉ። አፈናዉና እንግልቱ፣ መታሰሩና መገደሉ ቢበዛም ያንን ሁሉ በመቋቋም ሕዝባዊ ስብሰባዎች በመደረግ ላይ ናቸዉ።*

*በዚህ በግንቦት አሥራ አምስቱ ምርጫ 524 (በሶማሌ ክልል ያሉ 23 ቱን ሳይጨምር) የፓርላማ መቀመጫዎች ለዉድድር ይቀርባሉ። ገዢዉ የኢሕአዴግ ፓርቲን በዋናነት በመቀናቀን ትልቅ አማራጭ ሆኖ የቀረበዉ የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲን ያካተተዉ መድረኩ ነዉ። መድረኩ ከ524 ወረዳዎች ከሰላሳ ስድስቱ በስተቀር፣ በ485 ቱ ይወዳደራል። (በዘጠና ሰባት በ418 ወረዳዎች ነበር ቅንጅቱ የተወዳደረዉ) ቢያንስ ቢያንስ በኦሮሚያ ከ178 ወረዳዎች በ 175ቱ ፣ በአማራዉ ክልል ከ138 ወረዳዎች ቢያንስ በ125 ቱ፣ በደቡብ ክልል በሁሉም 123 ወረዳዎች፣ በትግራይ ከ38 ወረዳዎች ቢያንስ በ34 ቱ፣ በቤኔሻንጉል ከ9ኙ ወረዳዎች ቢያንስ በሁለቱ ፣ በአፋር ከስምንቱ ወረዳዎች ቢያንስ በአምስቱ፣ በጋምቤላ ከሶስቱ ወረዳዎች በሁለቱ፣ ከሃረሬ ከሁለት ወረዳዎች በአንዱ፣ በድሬደዋ በሁለቱም ወረዳዎች፣ በአዲስ አበባ በሃያ ሶስቱ ወረዳዎች ይወዳደራል።*

*ገዢዉ ፓርቲ ጠንካራ ተቃዋሚ እንዳይኖር ያደረገዉንና አሁን በማድረግ ላይ የሚገኘዉን ደባና ጸረ-ዲሞክራሲያዊ አሰራር የኢትዮጵያን ፖለቲካ በቅርበት የሚከታተል ሰዉ ይዘነጋዋል ብዬ አላስብም። ጠንካራ የተቃዋሚ አባላትና አመራሮች እየተገደሉና እየታሰሩ ናቸዉ።*

*በትግራይ በአድዋ አካባቢ መድረኩን ወክሎ ለፓርላማ የሚወዳደር፣ አረጋዊ ገብረዮሀንስ የሚባል ወጣት፣ የኢሕአዴግ ታጣቂዎች ናቸዉ በሚባሉ ተደብድቦ ተገድሏል። አሁን በትግራይ አክሱም አካባቢ በምትገኝ ዉቁሩ በምትባል ከተማ መድረኩን ወክሎ ለፓርላማ የሚወዳደር አያሌዉ አያለ የሚባል ሌላ ወጣት በታጣቂዎች ተደብድቦ ክፉኛ ተጎድቷል።*

*በነዚህ መድረኩን ወክለዉ በሚወዳደሩ ወገኖች ላይ ይህ አይነቱ አሰቃቂና አረመኔያዊ እርምጃ እየተወሰደ ያለዉ፣ ለሕወሃት ጀርባ እየሰጡ፣ ወደ አንድነትና ወደ አረና እየመጡ ያሉ የትግራይ ወገኖቻችን ሆን ብሎ ለማስፈራራት እንደሆነ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነዉ። ሰዉን በጉቦና በሸቀጣሸቀጥ ማሸነፍ ሳይቻል ሲቀር ወደ ጠመንጃና ወደ ጉልበት መሸጋገር ይሉታል ይሄ ነዉ።*

*አንጋፋ ወጣት የፖለቲካ ፓርቲ መሪ፣ የኢትዮጵያ አንሳ ሱንኪ፣ ብርቱካን ሚደቅሳ፣ አሳፋሪና ኢሰብዓዊ በሆነ መንገድ በግፍ እንድትታሰር ተደርጓል። ይህም የሆነበት ምክንያት አሳሪዎቿ እንደሚሉት ሕግ ጥሳ ሳይሆን፣ በርሷ መሪነት ከጠበቁትና ካሰቡት በላይ የሆነ፣ የሚያራምዱትን የጎሳ ፖለቲካ አፈር ድሜ የሚያስገባ፣ እነርሱ ለአገዛዝ እንዲያመቻቸዉ በዘር የከፋፈሉት ሕዝብ በኢትዮጵያዊነት ጥላ ሥር የሚያሰባስብ የሃያ አንደኛዉ ክፍለ ዘመን የሰለጠነ ፖለቲካ በማራመዷ ነበር። «እረኛ ሲመታ በጎች እንደሚበተሉ» አላማቸዉ የሰላማዊ ትግሉን መሪ በማሰር ብርቱካን*

*ሚደቅሳ የምትመራዉን ድርጅት ለመበተን ነበር። ነገር ግን አልተሳካላቸዉም። እንግዲህ አንድ በሉ።*

*አንድ ድርጅት ሁልጊዜ ስህተቶችን ይሰራል። በዉስጡም ልዩነቶች መፈጠራቸዉ አይቀርም። በአንድነት ፓርቲ ዉስጥ እንደ ማንም የፖለቲክ ድርጅት ልዩነቶች ታይተዋል። አንዳንድ ልዩነቶች በይፋ ለሕዝብ እንዲወጡ የተደረጉም አሉ። እነ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያምና አብረዋቸዉ ያሉ ጥቂት ወገኖች በአንድነት ፓርቲ አመርሮች ላይ ያለ ማቋረጥ ሲዘነዝሩት የነበረዉን ወቀሳና ትችት መቼም ሁላችንም የምናስታወሰዉ ነዉ። (ይመስለኛል ብዙ የሚያዳምጣቸዉ ጠፋ እንጂ አሁንም ትችታቸዉን ሳይቀጥሉ አልቀረም)*

*ገዢዉ ፓርቲ ማርክሲስትና ሚስጥራዊ አሰራር ስላለዉ በዉስጡ ያሉ ልዩነቶችን ማወቅ አይቻልም። ያ ብቻ አይደለም በፓርቲ ዉስጥ ካሉ ጥቂት ግለሰቦች ዉጭ የተለየ ሃሳብ ከመጣ ዉጤቱ መታሰር በመሆኑ ማንም የኢሕአዴግ አመራር አባል በራሱ ላይ ካልፈረደ በቀር ተቃዉሞ የሚያሰማበት ሁኔታ የለም። ከታመኑ ምንጮች ያሉን መረጃዎች እንደሚጠቁሙት አቶ አርከበ እቁባይ፣ አቶ አባይ ጸሃዬ፣ ዶር ቴዎድሮስ አዳኖም፣ አቶ ኩማ ደመቅሳ፣ አቶ ብርሃን ክርስቶስ (በአዉሮፓ ሕብረት የኢትዮጵያ አምባሳደር)፣ ዶር ሳሙኤል አሰፋ (በአሜሪካ የቀድሞ የኢትዮጵያ አምባሳደር) እንዲሁም በርካታ የኢሕአዴግ አመራር አባላት በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ላይ የተወሰደዉን እርምጃ የሚቃወሙና በአስቸኳይ መፈታት እንዳለባት የሚያምኑ ናቸዉ። ነገር ግን አቶ መለስ ለጋዜጠኞች «ታሳዝነኛለች» እንዳሉት ሳይሆን፣ በፍጹም ጭካኔ የተሞሉ በመሆናቸዉ፣ እነዚህ የኢሕአዴግ አመራር አባላት እኝህን ዴሞክራት መሳይ አምባገነን ሰዉ መጋፈጥ አልቻሉም። ይፈሯቸዋል።*

*እንግዲህ ኢሕአዴግ እንዲህ አይነት አሰራር እያለዉ ነዉ፣ የኢሕአዴግ ካድሬዎችና ፕሮፓጋንዲስቶች አይናቸዉን በጨዉ አጥበዉ፣ እነ ፕሮፌሰር መስፍን የሚያነሱትን ተቃዉሞዎችና በአንድነት ዉስጥ ተፈጠሩ የተባሉ ልዩነቶችን እያጋነኑ፣ መረጃዎችን እየለጠጡና አንዳንዴ ዉሸትን እየጨመሩ፣ ከፍተኛ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ በአንድነት ፓርቲ ላይ እየነዙ ያሉት። ነገር ግን አልተሳካላቸዉም። ሁለት በሉ።*

*የፕሮፓጋንዳ ዘመቻዉ በአንድነት ፓርቲ ዉስጥ ያሉትን ጥቃቅን፣ በአንድ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ ዉስጥ ሊኖሩ የሚገባቸዉን ልዩነቶችንን በማጋነን ላይ ብቻ የተመረኮዘ አልነበረም። የአንድነት ፓርቲ መድረክን ከተቀላቀለ ጀምሮ በመድረክ አባል ድርጅቶች መካከል ልዩነቶችን ለመፍጠር ተራና ርካሽ ወሬዎችን አፍቃሪ ወያኔ/ኢሕአዴግ ሜዲያዎች ሲያራግቡ እያየን ነዉ። አቶ ስዬ አብርሃ የአንድነት ፓርቲ በመቀላቀላቸዉ አረና ትግራይ እንዳዘነ፣ በዶር ነጋሶ ጊዳዳ ዉሳኔ ደግሞ እነ አቶ ቡልቻ ደመቅሳ እንዳኮረፉ፣ በነዶር በየነ ጴጥሮስና በአንድነት ፓርቲ መካከል በደቡብ ክልል ለፓርላማ የሚወዳደሩትን በመምረጥ ዙሪያ ክፍፍሎች እንደተፈጠሩ የሚገልጹና ሌሎች የዉሸት ዜናዎች በሰፋት ሲሰራጩ ሰንብተዋል። አሁንም አልተሳካላቸዉም። ሶስት በሉ።*

*(በነገራችን ላይ አይጋ ፎረምና ቤን የመሳሰሉ አፍቃሪ ኢሕአዴጎች መድረኩ ስብሰባ ሲያደርግ ስንት ወንበሮች እንደነበሩ ፣ የመሰብሰባዊያዉ አድራሽ ግድግድ ቀለሙ ምን እንደነበረ እንዳልተረኩልን ሁሉ ፣ ዛሬ በመድረኩ ከፍተኛ እጩ የፓርላማ ተወዳዳሪዎች ላይ በገዢው ፓርቲ ታጣቂዎች ኢሰባአዊና ኢፍትሃዊ ግድያና ድብደባ ሲፈጸም፣ ታላቅ የአፍሪካ መሪ እያሉ የሚያወድሷቸዉ አቶ መለስ ዜናዊ፣ ሌሎች ኢትዮጵያውያንን «ጠላትና እንክርዳዶች» እያሉ ሲጠሩና እንደ ተራ ዱርዬ ሲሳደቡ እየሰሙ ዝምታን የመረጡ አደርባዮች መሆናቸዉን እያየን ነዉ።)*

*የአንድነት ፓርቲና መድረኩ በተለያዩ የአገሪቷ ግዛቶች ከሕዝቡ ጋር እንዳይገናኙ ተደርገዋል። በአዳማ/ናዝሬት የኢሕአዴግ ካድሬዎች የአንድነትን ሕዝባዊ ስብሰባ ረብሸዋል። በአዲስ አበባ ከአምስት ጊዜ በላይ በመስቀል አደባባይ ስብሰባ ለማድረግ ተጠይቆ ገዢዉ ፓርቲ ተልካሻ የሆኑ ምክንያቶችን እየሰጠ ፍቃድ ከልክሏል። በርካታ የአንድነት ፓርቲ ጽ/ቤቶች እንዲዘጉ ለማድረግ*

ተሞክሯል። በርካታ የአንድነት አባላትና ደጋፊዎች ከሥራ ተባረዋል። ብዙዎች ታስረዋል። አንድነትን፣ ኢትዮጵያዉያን እንዳይደገፉ በየክልሉ ከፍተኛ ወከባና እንግልት እየደረሰ ነዉ። ብዙዎች ሕይወታቸዉን አጥተዋል።

በአንድነት ላይ እየደረሰ ያለዉ ጥቃት ከወያኔ/ኢሕአዴግ አካባቢ ብቻ አይደለም እየመጣ ያለዉ። ተቃዋሚ ነን የሚሉ በተለይም በዉጭ አገር የሚቀመጡ ወገኖችም ይገኙበታል። ከነዚህም መካከል በተለይም አፍቃሪ ግንቦት ሰባት ንቅናቄ፣ የሆኑት እንደ ከረንት አፌር የዉይይት መድረክ አይነቶችን መጥቀስ ይበቃል። እነዚህ ቡድኖች በተለይም በዉጭ አገር ያለዉን ኢትዮጵያዊ በማደናገር፣ ኢትዮጵያ ዉስጥ እየተደረገ ያለዉን እንቅስቃሴ ሰዉ እንዳይደገፈዉ ለማድረግ ይሄ ነዉ የማይባል አሉታዊ ሚና አውቀዉም ሆነ ሳያወቁ እየተጫወቱ ነዉ።

አማራጭ ሳይሰጡ፣ እነርሱን የሰሩትን የተጨበጠ ነገር ሳያሳዩ፣ በዉጭ አገር ተቀምጦ፣ በኢትዮጵያ ከህዝቡ ጋር ተኩኖ የሚደረግን እንቅስቃሴ፣ ትንሽ ትሁን ትልቅ፣ ማንኳሸሹ ይቅርታ ይደረግልኝና ግብዘነትና አሳፋሪ አድርጌ ነዉ የማየዉ። (ስለከረንት አፌር ፓልቶክ ክፍል ዘርዘር ያለ ዘገባ፣ እንዲሁም በቅርቡ ምርጫዉ በተመለከተ፣ መሰረቱ በአዉሮፖና በአሜሪካ የሆነዉና ከተቋቋመ ሁለት አመት በቅርብ ጊዜ የሚያከብረዉ፣ የግንቦት ሰባት ንቅናቄ፣ ላወጣቸዉ ጠቃሚ ያልሆኑ፣ አፍራሽ መግለጫዎች ምላሽን የያዘ ጽሁፍ ወደፊት ለአንባቢያን እናቀርባለን።)

እንግዲህ የአንድነት ፓርቲ እንዲሁም መድረኩ በዚህ አይነት እሳት ዉስጥ እያለፉም፣ በመጪዉ የ2002 ምርጫ ጠንካራ አማራጭ ሆነዉ መገኘታቸዉ በኢትዮጵያ ለዉጥ እንዲመጣ ለሚፈልግ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ትልቅ ደስታን ሊሰጥ የሚገባ ነዉ ባይ ነኝ።

የአንድነት ፓርቲ ያሰበዉንና ያቀደዉን ከግብ ላያደርስ ይችላል። እንደጠበቅነዉና ተስፋ እንዳደረገነዉ ነገሮች ግጥምጥም ላይሉ ይችላሉ። በድርጅቱ የሚያሳዝኑ ሁኔታዎች ልናይ እንችላለን። መነሳት እንዳለም መዉደቅ እንደሚኖር ማወቅ አለብን። የአንድነት ፓርቲ ወድቆ ያወቃል። የሰላማዊ ፖለቲካ ታጋዮች ወደ ኋላ ሄደዉ ያወቃሉ። ይሄ ሁሉ ያለ ነገር ነዉ።

ነገር ግን በአሁኑ ወቅት ከላይ የተዘረዘሩት ዱላዎች አያረፉባቸዉም የአንድነት ደጋፊዎችና አባላት ወድቀዉ እየተነሱ ፣ እጅ ሳይሰጡ፣ ተስፋ ሳይቆርጡ፣ መንቀሳቀስ መቻላቸዉ በራሱ ትልቅ ድል ነዉ ! ! ኢትዮጵያ ተስፋ እንዳላት የሚያሳይ ነዉ።

አንድ ድርጅት ጥንካሬዉ የሚለካዉ ማጥቃት በመቻሉ ብቻ አይደለም። ነገር ግን ሲጠቃም ጥቃትን መመከት በመቻሉም እንጂ።

የአንድነት ፓርቲ እንዲሁም መድረኩ ጥቃትን መክቶ፣ በአሁኑ ወቅት በማጥቃት ላይ ይገኛል። ወያኔ/ኢሕአዴግ በኔ ሥር ያሉ ናቸዉ በሚላቸዉ ቦታዎች ከፍተኛ ትንቅንቅ እየተደረገ ነዉ። የተቃዋሚዎች ማእከል በሆኑት በነአዲስ አበባ የሚደረገዉ እንቅስቃሴ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በኢሕአዴግ ማእከል በነበሩ እንደ ትግራይ ባሉ ቦታዎች እንቅስቃሴዎችን እያየን ነዉ።

እንደዚህም ሆኖ የሚያሳዝነዉ፣ በዉጭ አገር የምንኖረዉ ኢትዮጵያዊያን፣ በዘጠና ሰባት ያኔ ተቃዋሚዎችን እንደደገፍነዉ አሁን ድጋፋችንን እያበረከትን አለመሆናችን ነዉ። ይህ የሆነበት ምክንያት በዋናነት ተስፋ በመቁረጣችን ሲሆን በሁለተኛነት ደግሞ በዉጭ አገር ያሉ አንዳንድ ከተቃዋሚ ወገን ነን የሚሉ በሚያሰራጩት አፍራሽና ተራ የጥላቻ ፕሮፖጋንዳ ነዉ።

ይህ ሁኔታ መቀየር ያለበት ይመስለኛል። ሁላችንም ከስሜት ወጥተን ያሉትን ተጨባጭ ሁኔታዎች ቁጭ ብለን እንድናመዛዝን በአክብሮት እጠይቃለሁ። ቀኙን ግራዉን በመመልከት፣ ብዙ የሚያወሩ አሉና፣ እስቲ ሁሉንም በሥራቸዉ እንመዝናቸዉ።

ከሌሎች መጠበቅ ቀላል ነዉ። ሌሎች ይሄን ለምን አያደርጉም ብሎ መተቸት ቀላል ነዉ። በዉጭ አገር ተቀምጦ፣ ወይንም በፓልቶክ በሌላ ስም ገብቶ «የጀግንነት ቃላት ማዉራት፣ ዘራፍ ማለት» ቀላል ነዉ። በቦታዉ ሆኖ ቢሳካም ባይሳካም ለዉጥ ለማምጣት መጣር ግን ሌላ ነገር።

በአገር ቤት የሚደረገዉ ትግል ብርቱካን ሚደቅሳ ቃሊቲ ያስገባ፣ የወጣት አረጋዊ ገብረዮሐንስ ደም በአደዋ የረጨ፣ የአቶ አያሌዉን አጥንቶች በዉቂሮ የከሰከሰ፣ ወ/ሮ ገነት ባላቻ በዲላ ከሃያ አምስት አመት ሥራዋ እንድትባረር ያደረገ፣ የአቶ ዳንዔል ወልደገብርኤል የአሥራ ሁለት አመት ልጅን ያሳሰረ፣ ትልቅ መስዋእትነት እያስከፈለ ያለ ትግል ነዉ። በዚህ ትግል ዉስጥ መሳተፍ ጀግንነት ነዉ። እነዚህ ጀግኖች ድጋፋችን ያስፈልጋቸዋል። እነዚህን ጀግኖች ጀግኖች አይደሉም የምንል ከሆነ ታዲያ ማን ነዉ ጀግናዉ ? እነዚህን ጀግኖች ካልደገፍን ታዲያ ማንን ነዉ የምንደግዉ ? አሁን ካልደገፍናቸዉ መቼ ነዉ የምንደግፋቸው ?

አጠንክሬ የአንድነት ፓርቲ እንዲሁም መድረኩን እደግፋለሁ። በየአለም ዙሪያ ለተበተኑት ኢትዮጵያዉያን ወገኖቼ ድጋፋቸዉን እንዲለግሱም ጥሪ አቀርባለሁ። ፈረንጆች «Let not the perfect be the enemy of the good» ይላሉ። ሁኔታዎች ፍጹም እንደምንፈልገዉ ባለመሆናቸዉ ፊታችንን ከጥሩ ነገር አናዙር ማለታቸዉ ነዉ።

ኢትዮጵያ የኢንጂነር ግዛቸዉ ብቻ አይደለችም። ኢትዮጵያ የአቶ ስዬ ብቻ አይደለችም። ኢትዮጵያ የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ብቻ አይደለችም። ኢትዮጵያ የአቶ አረጋዊ ብቻ አይደለችም። ኢትዮጵያ የሁላችንም ናት።

እነ አቶ መለስ ዜናዊ በአገራችን ጉዳይ ተስፋ ቆርጠን ዝም እንድንል፣ የፈለጋቸዉን እያሰሩ፣ የፈለጋቸዉን እየገደሉ፣ የሕዝቡን ገንዘብ እየዘረፉ፣ እርስ በርሳችን እያናከሱን፣ ባርያ ሆነን እንድንኖር ነዉ የሚፈልጉት። «ሰዉ አለ ነጻነቱ ምንድን ነው» እንዳለች ብርቱካን ሚደቅሳ እኛም ለነጻነታችንና ለአገራዊ ክብራችን ዋጋ ለመክፈል መዘጋጀት ይኖርብናል። በተራ ወሬዎች የምንሸመደመድ ከሆነ ወገኖቼ የትም አንደርስም።

ትግል ቀልድ አይደለም። ቀበቶዎቻችንን እንታጠቅ። የኛ የሆነዉን እግዚብሄር ሲፈጠረን በጸጋ የተቀበልነዉን፣ አምባገነኖች በጉልበት የሰረቁብንን ማንነታችንና መብታችንን እናስመለስ !

እግዚብሄር ያከብርልኝ !